kidusl@yahoo.com

***የድል መንገድ***

*ኦባማ በአሜሪካ ውስጥ ትልቅ ተቀባይነትን ያገኘው ባነገበው የለውጥ ጥያቄ ነው:: ለውጡም በኢትዮጵያ ተመሳሳይ መሆን አለበት:: ይህ ትውልድ ከ60ዎቹ ትውልድ እንደሚሻል በ97ቱ ምርጫ እና ከዚያም በኃላ ባለው ጊዜ አሳይቷል:: ይህ ትውልድ እርስ በእርሱ ለመተላለቅ በኢትዮጵያ ታሪክ ከ97ቱ መርጫ የተሻለ ጊዜ አልነበረውም:: የ97 ምርጫ መሞት እንጂ አልሞ ተኳሽን መግደል ያልነበረበት ሟቹ ወጣት የወንድሙን ደም መበቀል ሳይፈልግ ቀርቶ አይደለም:: ገድሎ መሞት አቅቶት አይደለም የጥይት እራት ሲሆን ዝም ያለው:: መግደል የሚጀምረው እንዲሞት የሚፈልገውን ስርአት እና አስተሳሰብ አብሮ ለመግደል ነው:: አሁን የሚፈለገው የትግል መንስኤ አይደለም:: ኢትዮጵያ ውስጥ ለሀገሪቷ ልእልና ተብሎ የሚያታግል በደል ላለፉት አርባ አመታት ጠፍቶ አያውቅም:: ኢትዮጵያ ውስጥ አሁን የሚያስፈልገን የአመለካከት እና የአገዛዝ ስር ነቀል የሚያመጣ «ኦባማ» ነው::*

*ኢህአዴግ የማይወድቀው በጥንካሬው ሳይሆን በተቃዋሚዎች ድክመት ነው:: ድክመቱ የአለመተባበር ብቻ ሳይሆን የራእይ ድክመትም ነው:: ኦባማ የዘረኝነትን እንቅፋት ጥሶ፤ በአሜሪካ ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ መልኩ ወጣቱን ያሳተፈ ፖለቲካ ፈጥሮ አሸናፊ የሆነው የተለየ እና አብላጫውን በተለይ የወጣት ሀይል የሆነውን ወጣቱን ከኃላው ስላሰለፈ ነው:: «ጠላትህን ቀንስ ወዳጅህን አብዛ» የሚል መመሪያ ያለው ኦባማ በተለያዩ ጊዜዎች ሰዋዊ ስሜቶችን የሚፈትኑ ጥቃቶች ሲገጥሙት ያሳለፋቸው ጊዜያዊ ጥቅማቸው ከዘለቄታዊ ጥቅማቸው ጋር ተመዝነው ነው:: ለአብነት ያህል የቀድሞው ፕሬዚዳንት ቢል ክሊንተን የሳውዝ ካሮላይናን ድል ተከትሎ ስለ ኦባማ ሲጠየቅ «ጄሲ ጃክሰንም በ80ዎቹ አሸንፎ ነበር» ለሚለው ስላቃዊ ንግግሩ ኦባማ የሰጠው መልስ ከክሊንተን ጋር ለዘለቄታው የማያጋጨውን «ከሀያ አመት በፊት የነበረው ፖለቲካ እና የአሁኑ አንድ አይደለም» በሚል ሰላማዊ መልስ ነው::*

*ጠላታችንን በትክክል ለይተን ማስቀመጥ አለብን:: ጠላታችን አመለካከት አይደለም:: ጠላቶቻችን የአመለካከት ልዩነት ያሉን ሰዎች አይደሉም:: ጠላቶቻችን የጎረቤት አገሮች እና የጎረቤት አገር መሪዎች አይደሉም:: ጠላታችን ድህነት ነው:: ጠላታችን ውርደት ነው:: ለዚህ ሁሉ ተጠያቂ የሆነው ደግሞም የጠላታችን ፈጣሪ ኢህአዴግ ነው:: እዚህ ጋር ኢህአዴግ እና ወያኔ በሚሉ ስሞች መጣላት ወይም መነታረክ የለብንም:: ለዚህ አይነቱ የ«ቸ» እና «ሸ» ንትርክ ጊዜ የለንም:: የ«ቸ» እና «ሸ» የትግል ጊዜ አብቅቷል:: ይህንን ጽሁፍ ስጽፍ እናንተ ደግሞም ስታነቡ 10ሚሊዮኖች ርሀብ ላይ ናቸው:: ቁርሳችንን በልተን ምሳ ላይ ስንዘገይ ርሀብ ተሰምቶን ያውቅ ይሆናል:: ምናልባትም ምሳን ሳንበላ እራት ላይም ልንዘገይ እንችላለን:: ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ይሄ አይነት ርሀብ አይደለም:: 10ሚሊዮኖች የተራቡት ርሃብ ይሄ አይደለም:: 10ሚሊዮኖች ለወራት ነው እየተራቡ ያሉት:: ለአንድ ቀን መራብን ካወቅን ለወራት መራብ ምን እንደሚመስል መገመት አያቅተንም::*

*የ10ሚሊዮኖችን ርሃብ የፈጠረው የ80ሚሊዮኖች የዲሞክራሲ ፣ ፍትህ እና እኩልነት ርሃብ ነው:: የ80ሚሊዮኖችን ርሃብ የፈጠሩት ደግሞም ቢበዙ ሺ ኢህአዴጎች እና ጀሌዎቻቸው ናቸው:: እንቆቅልሽ አይደለምን? ሺዎች ሚሊዮኖችን ሲቆጣጠሩ?*

*ላለፉት አርባ አመታት በኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛ ደም ያፋሰሰ ለብዙ ዜጎች ህይወት መጥፋት የሆነ ፖለቲካ ተስተናግዷል:: በእነዚህ አርባ አመታት ውስጥ የፖለቲካው ምህዋር ፣ ፍልስፍናው እና አቅዋሙ አንድ ሆኖ ሳለ ፣ ሲጋደሉ የነበሩት ግን በተለያየ*

**ቡድን የተደራጁ የአንድ ዘመን እና አብዛኛዎቹ የአንድ ግቢ ተማሪዎች ናቸው:: በክፍሉ ታደሰ የተጻፈው «ያትውልድ» ፤ በጋዜጠኛ ገነት የተደረገው የኮ/ል መንግስቱ ኃ/ማርያም ቃለ-መጠይቅ «የኮ/ል መንግስቱ ትዝታዎች» በዘነበ የተጻፈው በኮ/ል መንግስቱ የስልጣን ህይወት ዙሪያ የተጻፈው «ነበር» መጽሃፍ ፤ በብርሃኑ ነጋ የተጻፈው «የነጻነት ጎህ ሲቀድ» እንደ አጭር ሪፈረንስ ወስደን የአርባ አመቱን የኢትዮጵያ ጉዞ ቃኝተን እርስ በራሳቸው በጥይት ሲጫረሱ የነበሩት ፤ አሳሪና ታሳሪ የነበሩት፤ አሳዳጅ እና ተሳዳጅ የነበሩት እኒህ የአንድ ግቢ ልጆች መሰረታዊ ልዩነት ወይም የሚያለያያቸውን ርእዮተ አለም ብንቃኝ የምናገኘውምንም ነገር የለም:: ሁሉም ቡድኖች የሚስማሙበት አንድ ነጥብ ቢኖር ኢትዮጵያ በከፍተኛ ድህነት ውስጥ እንደነበረች፤ የንጉሱ አስተዳደር የፈጠረው ድህነት ህዝቡ መሸከም ከሚችለው በላይ እንደሆነበት እና የሽክሙ መበርታት አመጽን እንደወለደ ነው:: በወቅቱ የነበረው ፍልሚያ አጀማመሩ የህዝቡን ህመም ለማከም ቢሆንም ቀጥሎ የነበረው ግን የስልጣን እና የታሪክ ሽሚያ ነበር:: በ«ቸ» እና «ሸ» ቃላት ልዩነት በጥይት የተጣበሰ ትውልድ ነው አሁንም ላለንበት ችግር ተጠያቂው:: መፍትሄው ደግሞም የሶስት ትውልድ እድል የተሰጠው የአርባ አመቱ ፖለቲከኞቻችንን ጡረታ ማውጣት ነው:: መድረኩም ፖለቲካውም ለጊዜው ባለቤት ይተው::**

**ጨለማውን የምንገፈው በብርሃን ሀይል ነው:: ሚሊዮኖች የናፈቁትን ብርሃን የማብራትን ያህል ታሪክ ከቶም የለም::**

"*If there is anyone out there who still doubts that America is a place where all things are possible, who still wonders if the dream of our Founders is alive in our time, who still questions the power of our democracy, tonight is your answer*," **Obama**

**ለአገሬ ይህንን አይነት በቅኝ አለመገዛታችንን ፤ አኩሪ የሶስት ሺህ አመት ታሪክ እንዳለን፤ ታሪካችን ርሃብ ሳይሆን ብልጽግና እና ስልጣኔ መሆኑን የምናሳይበት ቀን ሩቅ መሆን ፈጽሞ የለበትም::**